# ትዝብት – የሰሞኑ  እይታዬ

ሃምሌ 25  ቀን 2008  ዓ.ም.

01-08-2016

በትዝብት ዓምድ ሳቀርብ የነበረው ተከታታይ ጽሁፍ ለተወሰኑ ወራቶች ቢሰወርም አሁን በሰሞኑ ባየኋቸውና አሳሳቢ ሆነው ባገኘኋቸው አንዳንድ ሁኔታዎች ላይ ሃሳብ እንዲንሸራሸር ማድረጉ አስፈላጊ መስሎ ስለታየኝ እነሆ አምዴን ለዳግመኛ ንባብ እንድትበቃ ይገፔ ቀርቤአለሁ። ትንተናው የሚያጠነጥነው ለወራቶች በተለይም በሰሞኑ በአገራችን የሚካሄደውን ሕዝባዊ አመጽ አስመልክቶ በውጭ አገር በስደተኛ ስም የሚኖረው ወጣት ያለውን አገራዊ ስሜትና ተሳትፎ በሚመለከተውና ሰሞኑን በሆላንድ ውስጥ ከደንሃግ ወጣ ብላ በምትገኘው ሌይድሰከንዳም በተባለች አነስተኛ ከተማ(ትልቅ መንደር ማለት ይሻላል)  በተከናወነው የኢትዮጵያውያን የስፖርት በዓል ዙሪያ ይሆናል።

በዓለም ዙሪያ ተበትኖ የሚኖረው ኢትዮጵያዊ ቁጥር ከአራት ሚሊየን እንደማያንስ የሰሞኑ ጥናት ያመለክታል።ከዚህ ውስጥ አብዛኛው ከአርባ ዓመት በታች የሆነ ወጣትና ጎለምሳ ነው።በቀላሉ የማይገመትም አዛውንትና በዕድሜ የገፉ መኖራቸው አይካድም።ሁሉም በየአገሩ ሲገቡ ምክንያት ያደረጉትና የመኖሪያ ፈቃድ አግኝተው ኑሯቸውን የጀመሩት በአገራቸው በኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ስርዓት ሊያኖራቸው ባለመቻሉ፣መብትና ነጻነታቸው በመገፈፉ,ለህይወታቸው አደገኛ የሆነ ሁኔታ እንደተፈጠረ፣በፖለቲካ እምነታቸው እንደታሰሩና መከራ እንደደረሰባቸው የመሳሰለውን ምክንያት በመዘርዘር  እንደሆነ አይዘነጋም።ጥቂቶች በጋብቻ፣በትምህርት፣በሥራና በቤተሰብ ቅልቅል ከአገራቸው ለመውጣትና በውጭ አገር ለመኖር እንደቻሉም የሚካድ አይደለም።ሆኖም ግን ሁሉም የሚጋሩት ነገር ቢኖር አንድ አገር ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን ነው።

ይህን የጋራ እሴት በተለያየ መልኩ ሲያንጸባርቁ ይታያል፤በባህሉ፣በእምነቱ፣በማህበረሰብ ስብስቡ፣በድግሱ፣በሃዘንና ደስታው ተሰባስበው አብረው ያሳልፉሉ።ወፍ እንዳገሩ ይጮሃል እንዲሉ በያሉበት አገር ያደጉበትንና ይዘው የመጡትን ወግና ልማድ ሳይረሱ ከአዲሱና በእንግዳነት ከሚኖሩበት አካባቢ ባህልና ቋንቋ ጋር አዋህደው ለመኖር ይጥራሉ።ጥቂቶችም በጥረታቸውና በችሎታቸው ከተቀበላቸው አገር ተወላጅ በልጠውና ተሽለው የሃላፊነት ቦታ ለመረከብ በቅተዋል።ብዙዎችም ያገሩ ዜጋ በተሰለፈበት ሙያና ዕድልና ሁኔታ በፈቀደላቸው መስክ ተሰልፈው የበኩላቸውን አስተዋጽኦ ያደርጋሉ።ኑሯቸውን ይገፋሉ። ጥቂቶችም ለዝቅተኛ ኑሮና ስቃይ የተጋለጡ አልጠፉም።የአካልጉድለት ከደረሰባቸው ሌላ በልዩ ልዩ ሱስ ተጠምደው ከማህበረሰቡ የተገለሉ፣ቤት አልባ የሆኑ፣በአእምሮ መቃወስ ህመም በማገገሚያ ጣቢያና በወንጀል ተግባር በእስርቤት የሚማቅቁ ኢትዮጵያኖችም መኖራቸው አይካድም።

በውጭ አገር የተወለዱት ከሚኖሩበት ህብረተሰብ ጋር፣እንደ ነባሩ ያገሬው ሰው መስለውና ተቀላቅለው የመኖር ዘይቤን ወርሰዋል።በቤተሰብ ብርታት ያገራቸውን ቋንቋ ለመናገር የሚችሉት ጥቂቶች እየሆኑ መጥቷል። ሂደቱ ከቀጠለ ከሁለት ትውልድ በኋላ ከኢትዮጵያና ከኢትዮጵያዊነት ጋር የሚኖራቸው ንክኪ የሚከስም ይመስላል፣ቀለማቸው ሳይቀር እየተከለሰ ለመምጣቱ ምልክቶች እየታዩ ነው።አሁን ጥቁር አሜሪካውያን በወሬ ከአፍሪካ መምጣታቸውን እንደሚናገሩት ምናልባት ከኢትዮጵያውያን የተወለዱት የልጅ ልጆች ከአፍሪካ ወይም ከኢትዮጵያ እንደመጡ በቃል ደረጃ ሊናገሩ፤ወይም እስከነ አካቴው የሚረሱበት ደረጃ ላይ ይረሱት ይሆናል።ያንን ለነገው ትተን ወደዛሬው ፊታችንን መለስ አድርገን የወጣቱን አዝማሚያ ማየቱ የሚሻል ይመስለኛል።

አንድ አገር የእድገት ተስፋውና የመኖሩ ዋስትናው የሚለካው በወጣቱ ትውልድ ምግባርና አገራዊ ስሜት እንደሆነ የሚያጠያይቅ አይደለም።አገር ትውልድ እየተቀባበለ የሚኖርበት፣መስዋዕት ተከፍሎበት ለተተኪ ትውልድ የሚተላለፍ ክብር ያለው አንጡራ የወል ንብረት ነው።አገር የሌለው ሕዝብ ማለት ሲደክመው የሚያርፍበት ዛፍ(ጎጆ) የሌለው ወፍ ወይም ውሃው ደርቆበት የሚሞት አሣ ማለት ነው።

የአገርን ጥቅም ከአዲሱ ትውልድ ስንት ስንተኛው ያምንበታል?ለአገሩስ ጉዳይ የሚቆረቆረው ምን ያህሉ ነው? ብለን ብንጠይቅ መልሱን ለማግኘት አንቸገርም።እስከአሁን ድረስ የአገራችን ነጻነት ተከብሮ የኖረው የየዘመኑ ትውልድ በከፈለው መስዋእትነት ነው።

ያ መስዋእትነትና የአገር ነጻነት ምንም እንኳን አደጋው ቢያንዣብብበትም በአሁኑ ጊዜም ቢሆንሊጠፋ አልቻለም።ብዙ ወጣቶች በሚያምኑበትና በሚችሉት መንገድ አገራቸውን ከአደጋ ለመከላከል ቆርጠው ተሰለልፈዋል፣ ወራሪንና የአገር አንድነትን የሚቀናቀን የውጭና የውስጥ ጠላት ሲነሳ በመከላከል መስዋእት ሆነው ህይወታቸውን ሰጥተዋል፤አሁንም ለመስጠት ዝግጁ የሆኑና በየእስር ቤቱም የሚማቅቁ ብዙዎች ናቸው።ሁኔታ ፈቅዶላቸው ህይወታቸው ተርፎ በየአገሩ ለስደት ኑሮ የተገደዱትም ለሚገጥማቸው ችግርና ፈተና እጅ ሳይሰጡ ያገራቸውንና የወገናቸውን ጉዳይ፣የተሰደዱበትን ዓላማ ሳይዘነጉ በቻሉት አቅም እያበረከቱ ነው።የተወሰኑት ኢትዮጵያውያን በየአገሩ ተሰባስበው የወገናቸውን በደል ለውጭ ዓለም በማሰማት የተሳተፉ ሲሆን በአገር ቤትም ያለው ሕዝብ እስከ ጥርሱ የታጠቀ የመከላከያ ሃይል ያለውን ጨቋኝ ቡድን የሚመራውን መንግሥት እየተጋፈጠ ከዳር እስከዳር እየተዋደቀ ይገኛል።

በውጭ አገር ስደተኛ ነኝ ብሎ የመኖሪያ ፈቃድ ተሰጥቶት የሚኖረው አብዛኛው ኢትዮጵያዊ በተለይም ወጣቱ በዚህ አገር አድንና የሙብት ማስከበር ትግል ውስጥ ምን ያህል ድርሻ እንዳለው ብንመለከት የሚያሳፍርና የሚያሳዝን ሆኖ እናገኘዋለን።የመኖሪያ ፈቃድ ያገኘበትን ጉዳይና የሰጠውን ምክንያት ዘንግቶት ምን አገባኝ በሚል አቋም ከዳር ቆሞ የሚታየው ብዙ ነው።ከአገሩ የተሰደደው ለመዝናናትና ለአስረሽ ምችው ኑሮ እጁን እንደሰጠ፣ለአገርና ለወገኑ

ግዴለሽ እንደሆነ የሚያደርገውን አድራጎትና ምግባረ ብልሹነት ሲያዩት ያስደነግጣል።በአገር ጉዳይ ለመወያየት ስብሰባ ሲጠራ የሚገኘው አዲስ መጡ ሲሆን እሱም መኖሪያ ፈቃዱን ለማግኘት የፖለቲካ ተሳትፎውን በፎቶ ግራፍ ለማሳየት ሲል ነው።መኖሪያ ፈቃድ ካገኘ በኋላ “ፖለቲካና ኮረንቲ በሩቁ” ብሎ ድራሹን ያጠፋል።እንደውም በፖለቲካ የሚሳተፉትን እንደጠላትና የሰላም ጠር አድርጎ ይቆጥራቸዋል።ለእንደዚህ አይነቶቹ ስለሃገር፣ስለባህልና ታሪክ ማውራትና መጨነቅ ኋላ ቀርነት ነው።ትልቁ እውቀትና ዘመናዊነት በምንም መንገድ ይሁን በምንም ገንዘብና ንብረት ማግበስበሱ ነው።በፍቅረ ነዋይ የተለከፈው ከስርዓቱ የወረሰው በመሆኑ አይፈረድበትም።ሰው እንደመሪው ነው ይባል የለ!

ሰሞኑን እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር ከጁላይ 27 እስከ 30 ድረስ፣ለአራት ቀናት ያህል በሆላንድ አገር በተካሄደው በአውሮፓ የኢትዮጵያውያን የስፖርትና የባህል በዓል ላይ ያየሁትን ሌላው በቦታው ያልነበር እንዲያውቀው በጥቂቱ ላቅርብ። ይህ አይነት ዝግጅት በአውሮፓ ውስጥ ከተጀመረ አስራ አራት ዓመት አስቆጥሯል። ከእግርኳስ ውድድሩ በተጓዳኝ በየዓመቱ ከተለያዩት የአውሮፓ አገሮች፣ከኢትዮጵያና ከሰሜን አሜሪካ፣እንዲሁም ከመካከለኛው ምስራቅ የመጡ ኢትዮጵያውያንና ቤተሰባቸው ከዘመድ አዝማድና ጓደኛ ጋር ተገናኝተው አብረው መልካም ጊዜ የሚያሳልፉበት፣እንደእረፍትም የሚዝናኑበት ወቅት ነው።ጎን ለጎንም መንግሥት የማያውቀው የንግድ ስራ የሚጧጧፍበት የድንኳን ውስጥ ጉልት ገበያ እየሆነ መጥቷል።ማስተሳሰሪያ ክሩ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት ነው። ኢትዮጵያ ከሌለች ኢትዮጵያዊነትና የኢትዮጵያውያን የስፖርት በዓል የሚል ድግስ ሊኖር አይችልም።ስለሆነም ለኢትዮጵያ መኖር ሁሉም የየድርሻውን ማበርከት ይኖርበታል ማለት ነው።

በዚህ በዓል ላይ ከእስፖርቱ ውጭ የኪነት እንቅስቃሴዎች የሚካሄዱበት ወቅት ነው።በአብዛኛው የገበያ ድንኳን ውስጥ ለሽያጭ የቀረበው ከምግብ ጋር የተያያዘ ሲሆን በሁሉም ማለት ይቻላል ስኒ ተደርድሮ ጀበና ከበው ቡና እየጠጡ የሚያወሩ ብዙዎች ናቸው።ታዲያ ሁሉም ነገር እንዳማረበት ያልቃል ማለት አይደለም፤ግጭትና ንትርክ አልፎ አልፎ አልጠፋም። በበዓሉ አዘጋጆችና በንግድ ዘርፉ በተሳተፉት መካከል በተለይም በዳንኪራው ዙሪያ ውዝግብና የጥቅም ግጭት ተከስቶ እንደነበረ ውስጥ አዋቂዎች ይናገራሉ።የተሰባሰበው በሚመስለው የደስታ ዘርፍ ውስጥ እራሱን ለማስደሰት የሚችልበት ዕድል ተከፍቶለታል።ከመልካምና ከማይጎዱ እንቅስቃሴዎች በተጨማሪ አእምሮንና አካልን በሚጎዱ መስኮች የተሰማሩም ነጋዴዎች የሚታዩበት መድረክ ነው።አልኮል፣ጫት እንዲሁም አዲስ መጡ ሺሻ የሚባለው  የጋያ (ትምባሆ) ሱስ በግላጭ የሚስተናገድበት ቦታ ሆኗል።በዚህ የሺሻ ሱስ  የተለከፉት አብዛኛዎቹ  በየአረብ አገሩ ተሰደው የኖሩ ለጋ ወጣት ሴቶች በመሆናቸው የበለጠ ልብ ይሰብራል።፣

የተለያዩትን ጎጂ ሱሶች በእስፖርቱ ሜዳ ዙሪያ በተተከሉት ድንኳኖች እንዲከናወኑ የፈቀደው የእስፖርት ፌዴሬሽኑ በመሆኑ ከገንዘብ በቀር ሌላ ማህበረሰብአዊ ደህንነትንና ጤናን በማስከበሩ እረገድ ፍላጎት የሌለው ሆኖ

ታይቷል።እስፖርት ለጤና መሆኑ እየታወቀ ፣ያንን የሚጻረሩ ድርጊቶች መፍቀድና ድንኳን አከራይቶ ከንግድ ገቢው እጠቀማለሁ ማለት በወገን ጉዳት ላይ እየነገዱ ወጣቱ ለአደጋ ሲጋለጥ በምን ቸገረኝነት መመልከትና ማበተረታታት ነው።እንደ ነጻነትና ስልጣኔ መቆጠር የለበትም።

በዚህ ወቅት ስለአገራቸው የወቅቱ ሁኔታ የሚጨነቁ ድርጅቶችና ግለሰቦች ተሰባስበው የሚወያዩበትም አጋጣሚ ነበር።በዚህ በሆላንዱ ዝግጅት ወቅት በአውሮፓ የኢትዮጵያውያን የውይይት መድረክ(ፎረም) በሚል ስያሜ የሚንቀሳቀሰው አካል ስብሰባ አዘጋጅቶ ነበር።በስብሰባው ላይ ከወደፊቱ እይታ ጠቃሚ እርእሶች ማለትም ኢትዮጵያዊነት የብሔር/ብሔረሰብ ጥያቄና ፌዴራሊዝም(በዶር.ፈቃዱ በቀለ)፣የማንነት ፖለቲካ ጠንቆችና አኗኗር የአብሮነት መፍትሔ ፍለጋ (በአቶ የሱፍ ያሲን) የቀረቡ ሲሆን ለወቅቱ ችግር ማለትም አሁን በአገራችን ውስጥ ከዳር እስከዳር በተቀጣጠለው ሕዝባዊው አመጽ ላይ ግን ትኩረት የሰጠ ውይይት አልነበረም።

በዚህ ስብሰባ ላይ ከሰላሳ የማይበልጡ ታዳሚዎች ሲገኙ በስፖርት ሜዳው ውስጥ፣ በዙሪያው በተተከሉ የምግብ፣የጫት፣የቡና፣የመጠጥ፣የሺሻ፣የሸቀጣ ሸቀጥ ድንኳኖች ውስጥ ግን በሺህ የሚቆጠር ኢትዮጵያዊ ይርመሰመስ ነበር። የሚሆነውን አጢኖ ለተከታተለውና ለተመለከተው ስደተኛ ነኝ የሚለው ወገን አገሩ ኢትዮጵያ በቀውስ ውስጥ መኖሯን የዘነጋ ወይም ደንታ የማይሰጠው የራሱንም ስደተኝነት የረሳ ይመስላል።በጣም የሚያስገርመው ደግሞ የውይይት ስብሰባ ያዘጋጁት ወገኖች ስብሰባ መኖሩን ለማስታወቅ የሜዳውን ድምጽ ማጉሊያ እንጠቀም ብለው ላቀረቡት ጥያቄ አዘጋጆቹ "ይህ የእስፖርት እንጂ የፖለቲካ ሜዳ አይደለም"ብለው መከልከላቸው ነው።ታዲያ ኢትዮጵያውያን የተሰበሰቡበት የስፖርት ሜዳ በዚህ አሳሳቢ ወቅት ስለአገራቸው ጉዳይ እንዳያውቁ፣በአገራቸው ጉዳይም ላይ በውይይት እንዳይሳተፉ መከላከልና ኢትዮጵያኑን በሚጎዳ ለጫት፣ለአልኮልና ለሲሻ ገበያ ማስፋፊያ እንዲሆን ቅድሚያ መስጠትና መፍቀዱ የጤነኛ አስተሳሰብ ነው?ከስደተኛስ ይጠበቃል?ይህን የስፖርቱ አዘጋጆች መልስ ሊሰጡበት ይገባል።የኢትዮጵያ ሕዝብ በጨቋኝ ስርዓት ላይ እምቢ ብሎ ሲነሳ ፣መስዋእትነት እየከፈለ ባለበት ወቅት አለመተባበርና አለመደገፍ ከጨቋኙ ስርዓት ጋር ከመወገኔላ ትርጉም የለውም።በደፈናው ፖለቲካና እስፖርት የተለያየ ነው ብሎ ከአገር ጉዳይ እራስንና ሌላውን ማግለል ከአንድ የስደተኞች ስብስብ የሚጠበቅ አይደለም።እስፖርተኛ አገረቢስና ስለአገሩ የማያስብ ከኧስ የተወለደ ልዩ ፍጡር ተደርጎ እስካልተቆጠረ ድረስ የተሰጠው ምክንያት ውሃ አይቋጥርም።

ይህን አይነቱን አዝማሚያና አድራጎት፣በመካከላችን ያለውን ድክመት አሶግደን ለተወለድንባትና ለመኖሪያ ፈቃድ ሰበብ ላደረግናት አገርና ለቁም ነገር ላበቃን ሕዝብ ውለታ የምንከፍልበትን መንገድ ብንከተል ለወጣቱ ትውልድም ምሳሌ ብንሆን ጠቃሚ ነው።ወጣቱን ትውልድ በሚቀጥፉ ጎጂ ልማዶችና አድራጎቶች እንዳይጠመድ ማህበረሰባዊ መፍትሄ ሊፈለግበት ይገባል።በነጻነት ስም ወጣቱ ትውልድ ገደል ሲገባ እያዩ አበጀህ!ቀጥልበት!

አይባልም።በአመለካከትና በዕድሜ በሰል ያለው ወገንም የመጣበትን አስታውሶ ለአገሩ ጉዳይ ቦታ ሊሰጠውና በአገር ውስጥ የሚካሄደውን አገር አድን ሕዝባዊ ትግል መርዳትና ማገዝ ይገባዋል።ምንም እንኳን በግል ኑሮው ላይ ማተኮሩ የኑሮ ግዴታ በመሆኑ የሚያስወግዘው ባይሆንም ጎን ለጎን ከአንድ ዜጋ የሚጠበቅበትን ማበርከት ተገቢ ነው።

ጥቂት የማይባለው ኢትዮጵያዊ አሰደደኝ ከሚለው መንግሥት ተወካይ ቢሮ(ኤምባሲ) ደጃፍ እየተደረደረ ህሊና ቢስ ሆኖ ከደሃ ወገኖቹ እየተነጠቀ በሚቸበቸበው በመሬት ቅርምቱ በመሳተፉ ይቅርታ የማይገባው ጥፋት በመፈጸም ላይ ይገኛል።ይህ የጥፋትና በደሃው ሕዝብ ላይ በሚፈጸም ወንጀል ተባባሪነት እንጂ ለእድገትና ለልማትም አስተዋጽኦ ማድረግ አይደለም።በዚህም አላበቃም፤በስርዓቱ የሚፈጸመውን ግፍና በደል እንደሌለ በመካድ አደባባይ ወጥቶ የስርዓቱ አወዳሽና ተከላካይ በመሆንም ያዙኝ ልቀቁኝ የሚል ስደተኛም አልጠፋም።ምርጫው የየግለሰቡ ቢሆንም ሕዝብና አገር ለመበደልና ለመበታተን ሌት ተቀን ከሚሠራ አምባገነን ቡድን ጋር መሰለፍ ብሔራዊ ክህደት እንደሆነና እንደሚያስጠይቅም ሊታወቅ ይገባል።በስርዓቱ የሚኮራና የሚተማመን ሰው የስደተኛ ካርዱን መልሶ ወደ አገሩ ቢመለስ ይሻለዋል።ይህ ስርዓት መውደቁ አይቀርም፣ይወድቃል።አሁን እያንዳንዱ የሚወስደው አቋምና የሚፈጽመው ተግባር ወደፊት የሚያፍርበት ወይም የሚኮራበት ይሆናል።

በዘንድሮው የሰሜን አሜሪካኑ(በቶሮንቶ ከተማ)የእስፖርት በዓል ላይ ባለመገኘቴ ልተችበት አልችልም።በቦታው የነበሩ ትዝብታቸውን ቢያካፍሉ መልካም ነው። ለሚመጣው ዓመት በሰሜን አሜሪካም ሆነ በአውሮፓ በሚዘጋጁት የስፖርት በዓላት ላይ እስከአሁን ድረስ የታዩ ጥፋቶችና ድክመቶች ታርመውና ተወግደው፣የአገራችንን ጉዳይ ባካተተ መልኩ እንደሚከናወን ተስፋ አደርጋለሁ፤የዛ ሰዎች ይበለን።

እግረመንገዴን ከሰሞኑ እይታዎቼ የመድረክ መሪ ዶር.መረራ ጉዴናና የሰማያዊ ፓርቲ መሪ ኢንጅነር ይልቃል በአሁኑ ጊዜ አሜሪካን አገር ውስጥ መገኘታቸውን ተገንዝቤአለሁ።በአሁኑ ጊዜ ደግሞ በአገራችን ውስጥ የጦፈ ሕዝባዊ አመጽ እየተካሄደ ነው።አወጣጣቸው የውጪን ለመቀስቀስ ፣የገንዘብ እርዳታ ለመሰብሰብ ወይስ የአሜሪካንን መንግሥት ለመማጸን? ወያኔን ለማዳን ወይም በተመሳሳይ ስርዓት ለመተካት ከአሜሪካኖች ጋር ውል እንደማይገቡ ተስፋ አደርጋለሁ።

አገሬ አዲስ

http://www.ethiopanorama.com